የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 22
ADDIS ABABA 8th January 2013

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፸፱/፪ሺ፭ ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.........ገጽ ፮ሺ፯፻፴፬

## CONTENTS

Regulation No. 279/2012

Ethiopian National Accreditation Office Re-Establishment Council of Ministers Regulation………………… Page 6734

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸፱/፪ሺ፭

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል::

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸፱/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩/ "አክሬዲቴሽን" ማለት አንድ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የተወሰነ የተስማሚነት ምዘና ተግባር ለማከናወን የሚያስችል ብቃት ያለው መሆኑን በሚመለከት የሚሰጥ ምስክርነት ነው፤

፪/ "የተስማሚነት ምዘና" ማለት ምርት፣ የስራ ሂደት፣ የአሠራር ስርዓት፣ ሰው ወይም ድርጅት የሚመለከቱትን ደረጃዎችንና መስፈርቶችን ማሟላቱን ማረጋገጥ ነው፤

፫/ "የተስማሚነት ምዘና አካል" ማለት አክሬዲቴሽን ሊሰጠው የሚችል የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት የሚሰጥ አካል ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 279/2012

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN NATIONAL ACCREDITATION OFFICE

This Regulation is issued by the Council of Ministers in accordance with Article 5 and Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Ethiopian National Accreditation Office Re-establishment Council of Ministers Regulation No. 279/2012".

### 2. Definitions

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "accreditation" means attestation related to a conformity assessment body conveying formal demonstration of its competence to carry out specific conformity assessment tasks;

2/ "conformity assessment" means demonstration that specified requirements relating to a product, process, system, person or body are fulfilled;

3/ "conformity assessment body" means a body that performs conformity assessment services and that can be the object of accreditation;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.75

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፬/ "የክትትል ግምገማ" ማለት አክሬዲቴሽን የተሰጣቸው አካላት የብቃት ደረጃቸውን ጠብቀው እየሰሩ ስለመሆኑ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በየወቅቱ የሚደረግ ግምገማ ነው፤

፭/ "ብሔራዊ የጥራት መሠረተ ልማት" ማለት በደረጃዎች ዘርፍ፣ በሜትሮሎጂ ዘርፍ፣ በተስማሚነት ምዘና እና በአክሬዲቴሽን ዘርፍ የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት ነው፤

፮/ "ሚኒስቴር" ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፤

፯/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል::

## ፫. እንደገና መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የአክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት (ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤት" እየተባለ የሚጠራ) ሀጋዊ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል::

፪/ የጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል::

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የጽሕፈት ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል::

## ፭. ዓላማ

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል:-

፩/ ዓለም ዓቀፍ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ብሔራዊ የአክሬዲቴሽን ሥርዓትን በመገንባት የአገሪቱ ምርቶችና አገልግሎቶች በአገር ውስጥ ገበያና በዓለም ገበያ ተቀባይነትና ተወዳጅነት እንዲኖራቸው የበኩሉን አስተዋፆ የማድረግ፤ እና

፪/ በአገር ውስጥ የሚሰጥ የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት ዓለም ዓቀፍ እውቅና እንዲያገኝ ለማድረግ የሚያስችል የአክሬዲቴሽን ስርዓት መመስረትና ተግባራዊ የማድረግ::

## ፮. ሥልጣንና ተግባር

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ ለተስማሚነት ምዘና አካላት አግባብነት ባላቸው ብሔራዊና ዓለም ዓቀፋዊ መስፈርቶች መሠረት የአክሬዲቴሽን አገልግሎት የመስጠት፤

፪/ የብሔራዊ አክሬዲቴሽን ምልክትን ቅርጽና ይዘት የመወሰንና በምልክቱ የመጠቀም ፈቃድ የመስጠት፤

4/ "surveillance audit" means a periodic audit performed to ensure that accredited bodies still meet their competence requirements;

5/ "national quality infrastructure" means a system established for standardization, metrology, conformity assessment and accreditation;

6/ "Ministry" means the Ministry of Science and Technology;

7/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Re-establishment

1/ The Ethiopian National Accreditation Office (hereinafter the "Office") is hereby re-established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Office shall be accountable to the Ministry.

## 4. Head Office

The Office shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as necessary.

## 5. Objectives

The Office shall have the objectives to:

1/ contribute its part for the acceptance and appreciation of Ethiopian products and services in domestic and international markets by developing appropriate infrastructure of national accreditation system compatible with international requirements; and

2/ establish and implement accreditation system which allows locally provided conformity assessment services to be recognized internationally.

## 6. Powers and Duties

The Office shall have the powers and duties to:

1/ provide accreditation service to conformity assessment bodies based on national and international requirements;

2/ determine the shape and other features of the national accreditation symbol and authorize its use;

፫/ አክሬዲቴሽን በተሰጣቸው አካላት ላይ የክትትል ግምገማ የማካሄድ፤

፬/ አክሬዲቴሽን የተሰጣቸውን፣ የታገደባቸውንና የተሰረዘባቸውን አካላት ዝርዝር መዝግቦ የመያዝና ለሕዝብ ግልጽ የማድረግ፣ እንዲሁም ለሚመለከታቸው የሕግ አስፈፃሚ አካላት የማስተላለፍ፤

፭/ የአክሬዲቴሽን ሂደት የሚመራበትን በተለይም አመልካቾች የሚገመገሙበትንና አክሬዲቴሽን የሚሰጥበትን፣ የሚታገድበትንና የሚሠረዝበትን እንዲሁም ከነዚሁ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትን ሥርዓት የሚመለከቱ መመሪያዎች የማውጣትና በሥራ ላይ የማዋል፤

፮/ እንደአስፈላጊነቱ የባለድርሻ አካላትን ያካተተ የምክክር መድረክ የማቋቋም፤

፯/ ለብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት መጠናከር የተቀናጀ ድጋፍ መኖሩን ለማረጋገጥ ተገቢነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የመሥራት፤

፰/ አክሬዲቴሽንን በሚመለከት በዓለም ዓቀፍ መድረክ የአገሪቱን ጥቅም መወከልና አገሪቱ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸውን ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊነት የመከታተል፤

፱/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤

፲/ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋልና በራሱ ስም የመክሰስና የመከሰስ፤

፲፩/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

፯. <u>የጽሕፈት ቤቱ አቋም</u>

ጽሕፈት ቤቱ፡-

፩/ የአክሬዲቴሽን ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

፰. <u>የምክር ቤቱ አባላት</u>

ምክር ቤቱ አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ አካላትና ከግሉ ዘርፍ ተውጣጥተው በመንግሥት የሚሰየሙ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከ፲፫ የማይበልጡ አባላት ይኖሩታል፡፡ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር በምክር ቤቱ ስብሰባዎች በአባልነትና በፀሐፊነት ይሳተፋል፡፡

3/ conduct surveillance audit on those bodies that have been accredited;

4/ keep a register and publicize the list of accredited bodies and those whose accreditations have been suspended and withdrawn, and forward same to the concerned regulatory bodies;

5/ issue and implement directives governing the accreditation process, in particular, the assessment of applicants and the granting, suspending and withdrawing of accreditations, and handling of grievances relating thereto;

6/ organize consultative meetings of stakeholders, as may be necessary;

7/ work in cooperation with the relevant stakeholders to ensure the existence of an integrated support for strengthening the national quality infrastructure;

8/ represent the country's interest in international forums regarding accreditation and follow up the implementation of treaties to which Ethiopia is a party;

9/ charge fees for the services it renders in accordance with the rate approved by the government;

10/ own property, enter in to contract, sue and be sued in its own name;

11/ carry out other related activities necessary for the attainment of its objectives.

7. <u>Organization of the Office</u>

The Office shall have:

1/ a Council of Accreditation (hereinafter the "Council");

2/ a Director General and, as may be necessary, a Deputy Director General to be appointed by the government; and

3/ the necessary staff.

8. <u>Members of the Council</u>

The Council shall have members not more than 13 in number, including the Chairperson, to be drawn from the relevant government bodies and the private sector and be appointed by the government. The Director General shall participate in meetings of the Council as member and secretary.

## ፱. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በጽሕፈት ቤቱ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የአክሬዲቴሽን ስትራቴጂን በመገምገም ያፀድቃል፤

፪/ ከባለድርሻ አካላት የሚነሱ ከአክሬዲቴሽን ጋር ተያያዥነት ባላቸው የፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳዮች ጽሕፈት ቤቱን ያማክራል፤

፫/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮(፭) መሠረት በጽሕፈት ቤቱ የሚወጡ መመሪያዎችን መርምሮ ያጸድቃል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከተው የጽሕፈት ቤቱ መመሪያ መሠረት አክሬዲቴሽንን በሚመለከቱ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡለትን ይግባኞች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

፭/ ጽሕፈት ቤቱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚጠየቁ የክፍያ ተመኖችን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

## ፲. የምክር ቤቱ ስብሰባ

፩/ ምክር ቤቱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔ የሚተላለፈው ከአባላቱ በአብዛኛው ድምፅ ሲደገፍ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፩. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የጽሕፈት ቤቱን ሥራ ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ላይ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የጽሕፈት ቤቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የጽሕፈት ቤቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

## 9. Powers and Duties of the Council

The Council shall have the powers and duties to:

1/ review and approve accreditation strategies developed by the Office;

2/ consider policy and strategic issues raised by stakeholders relating to accreditation and advise the Office accordingly;

3/ review and approve directives to be issued by the Office pursuant to Article 6(5) of this Regulation;

4/ examine and decide on appeals, lodged in accordance with directive of the Office referred to in sub-article (3) of this Article, against decisions with respect to accreditation;

5/ review, and forward its recommendation on, the rate of fees to be charged for the services of the Office.

## 10. Meetings of the Council

1/ The Council shall meet every three months; provided, however, that it meet at any time where necessary.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Council are present at any meeting.

3/ Decisions of the Council shall be made by majority votes; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its own rules of procedure.

## 11. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Office and shall direct and administer the activities of the Office.

2/ Without limiting the generality stated under sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Office specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the Office in accordance with the federal civil service laws and, in the case of employees engaged in the core functions of the Office, in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

ሐ) የጽሕፈት ቤቱ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ጽሕፈት ቤቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፤

ረ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለጽሕፈት ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## ፲፪. በጀት

የጽሕፈት ቤቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

## ፲፫. የሂሳብ መዛግብት

፩/ ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## ፲፬. የተሻረ ደንብ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ደንብ ቁጥር ፩፻፺፭/፪ሺ፫ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

## ፲፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

c) prepare the work programs and budgets of the Office and implement same upon approval;

d) effect payments in accordance with the budget approved for the Office;

e) represent the Office in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Office.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Office to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Office.

## 12. Budget

The Office's budget shall be allocated by the government.

## 13. Books of Accounts

1/ The Office shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Office shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

## 14. Repealed Regulation

The Ethiopian National Accreditation Office Establishment Council of Ministers Regulation No.195/2010 is hereby repealed.

## 15 Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 8th day of January, 2013.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**